Amharic | አማርኛ



# በቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ ውስጥ ደህና መሆን

የቅድመ ልጅነት ጊዜ ትምህርት እና እንክብካቤን በመጠቀም ለወላጆች እና ተንከባካቢዎች መመሪያ። ይህ ትንሽ መጽሓፍ ጥሩ እንክብካቤ ምን እንደሚመስል፣ ምን እንደሚጠይቁ እና የሆነ ነገር ትክክል ካልሆነ እንዴት መናገር እንደሚችሉ እንዲረዱት ተብሎ የወጣ ነው።

የጋራ ተነሳሽነት

Body Safety Australia

GENWEST

GENWEST የቪክቶሪያ መንግስትን ድጋፍ መቀበሉን አረጋግጧል

VICTORIA State Government

# ስለ ደራሲዎቹ

**የሰውነት ደህንነት አውስትራሊያ/Body Safety Australia** ልጆች ፍትሃዊ እና አክብሮት ያላቸው ግንኙነቶች ተፈጥሮ የሚደሰቱበት የልጅነት ጊዜን ከጥቃት ነጻ እንዲሆን ያበረታታል።

በቤት ውስጥ እና በትምህርት ቤት አካባቢ፣ ከመስመር ውጭ እና በመስመር ላይ በልጆች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመከላከል በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ፕሮግራሞችን ለልጆች፣ ለታዳጊ ወጣቶች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች እናቀርባለን። በኦንላይን መስመር ውጭና በመስመር ላይ።

የበለጠ መርጃ ለማግኘት ድረገጽ፡ **www.bodysafetyaustralia.com.au**

---

**GenWest** በመልበርን ምዕራብ በቤተሰብ እና በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት ይሰራል።

በማህበራዊ እና በጤና ትምህርት ፕሮግራሞች አማካኝነት ሰዎች እና ማህበረሰቦች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የሆነ ህይወት እንዲኖሩ እንደግፋለን።

እንዲሁም የቤተሰብ ጥቃት ያጋጠማቸው አዋቂዎች እና ህጻናት ደህንነታቸውን እንዲጠብቁ እና የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ እንዲያገኙ እንደግፋለን።

በበለጠ ለማወቅ በድረገጽ **genwest.org.au** ላይ ይጎብኙ

ምዕራፍ 1

# የእንክብካቤ ዓይነቶች እና ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት አቅራቢዎች።

አዋቂዎች ጥሩ እንክብካቤ ሰጪ (መዋእለ ህጻናት) ምን እንደሚመስል ሲያውቁ ልጆች በጣም ደህና ናቸው። ይህ ምዕራፍ የቅድመ ልጅነት ጊዜ ትምህርት እና እንክብካቤ (መእለ ህጻናት) ዓይነቶችን እና ምን እንደሚጠብቁ ያብራራል።

## የእንክብካቤ ዓይነቶች

| TYPE OF | ይህ ምንድን ነው | ምን ያካትታል |
|---|---|---|
| የረጂም ቀን እንክብካቤ | ይህልጅዎ ወደ ማእከሉ በአብዛኛዎቹ ቀናት ይሄዳል። | ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ የሚሰጥ እንክብካቤ። ልጆች እዚያ ይበላሉ፣ ይጫወታሉ፣ ይማራሉ እና ያርፋሉ፣ አብዛኛውን ጊዜ ከሌሎች ተመሳሳይ እድሜ ካላቸው ልጆች ጋር። አስተማሪዎች ብቃት ያላቸው ሙያተኛ ናቸው። |
| የቤተሰብ መዋእለ | በተመዘገበ (ፈቃድ ያለው) አስተማሪ በአንድ ትንሽ ቤት ውስጥ የሚሰጥ እንክብካቤ። | ልጆች በትንሽ ቡድን ውስጥ እንክብካቤ ይደረጋል፤ ብዙውን ጊዜከተደባለቀ ዕድሜ ጋር በመሆን። አስተማሪዎች የብቃት ሙያ ያላቸው ናቸው። |
| የክፍለ ጊዜ መርሃግብሮች/ አልፎ አልፎ የሚሰጥ እንክብካቤ | ለጥቂት ሰዓታት ወይም ቀናት እንክብካቤ፣ በእያንዳንዱ ቀናት አይደለም። | የአጭር ጊዜ ፕሮግራሞች፣ አንዳንድ ጊዜ በአንድ ማእከል ወይም በማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታ። ብዙውን ጊዜ የተደባለቀ እድሜ ያላቸው ኣነስተኛ መጠን ቡድኖች። አስተማሪዎች ብቃት ያላቸው ሙያተኛ ናቸው። |
| በዘመድ እንክብካቤ | በቤት ውስጥ እንክብካቤ በቤተሰብ አባል የሚሰጥ። | ልጆች በአንድ የተለመደ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ይደረጋል። ወላጆች በደህንነት ዙሪያ ያሉ ድንበሮች እና የሚጠበቁ ነገሮች ግልጽ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። |

## ወላጆች ሊጠይቋቸው የሚችሏቸው ሦስት ነገሮች

ልጄን ማን ነውየሚንከባከብ?

ሁሉንም አስተማሪዎች የማግኘት እና ከልጄ ጋር ማን እንዳለ የማወቅ መብት አለኝ።

እንዴት ነው የልጆችን ደህንነት የምትጠብቁት?

ልጆችን ለመጠበቅ ምን አይነት ደንብ ህጎችን እንደምትከተሉ እና የሚወሰድ እርምጃዎችን የማወቅ መብት አለኝ።

የሆነ ነገር ትክክለኛ ካልሆነስ?

የሆነ ችግር ከተፈጠረ ወይም የሚያሳስብኝ ከሆነ ምን እንደሚፈጠር የማወቅ መብት አለኝ።

## መጸዳዳትና እና ልብስ መቀየር

### ተገቢ የሆነው ምንድ ነው

- አስተማሪዎች በግል ቦታ እርዳታ ይሰጣሉ።
- ረጋ ብለው እና ገር ሆነው ይቆያሉ፣ እና ልጁን ያናግሩታል።
- ምን እያደረጉ እንደሆነ እና ለምን እንደሆነ ያብራራሉ።
- ልጁን የሚነኩት ሲያስፈልግ ብቻ ሆኖ ደህንነታቸው፣ ጤናቸው እና ንጽህናቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ ነው።
- ልጆች ለራሳቸው የሚችሉትን እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

### ተገቢ ያልሆነው ምንድ ነው

- አዋቂዎች ልጁን ከሚያስፈልገው በላይ መንካት የለባቸውም።
- ልጆች መጸዳጃ ቤት ሲጠቀሙ ወይም ልብስ ሲቀይሩ ከክትትል ውጭ መተው የለባቸውም።
- ልጆች ሁል ጊዜ ቢያንስ በሁለት አስተማሪዎች እይታ ውስጥ መሆን አለባቸው።
- አስተማሪዎች ህጻኑን የሀፍረት፣ የፍርሀት እና የመሳቀቅ ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ የለባቸውም።
- ልጆች ግላዊነትን ከፈለጉ በር ወይም መጋረጃ ያለው መጸዳጃ ቤት መጠቀም መቻል አለባቸው።
- ልጆች የሚችሉ ከሆነ የራሳቸውን ቂጥ እንዲጠርጉ መበረታታት አለባቸው።

*ለወላጆች ጠቃሚ ምክሮች:*

- የመጸዳጃ ቤት እና ዳይፐር መቀየር እንዴት እንደሚደረግ የመጠየቅ መብት አልዎት።
- ስለ የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች (ልምዶች) አስተማሪውን ለማነጋገር መጠየቅ ይችላሉ።
- ስለ አስተማሪው ባህሪ ካሳስብዎት ከዳይሬክተሩ ጋር ጉዳዩን የማንሳት መብት አልዎት።

## ለልጅ-አስተማማኝ ልምምድ ምን ይመስላል



**ጥሩ የህጻናት እንክብካቤ ማእከል:**

- ልጆችን ሁል ጊዜ ቢያንስ በሁለት ብቁ ባለሙያ ጎልማሶች እንዲቆጣጠሩ ማድረግ።
- የልጆች ደህንነት የስነ-ምግባር ደንብ እንዳለ እና ይህን መከታተል ።
- በሙያ ብቁ የሆኑ ሰራተኞች አሉት፣ ይህም በአሁኑ ጊዜ ከህጻናት ጋር የመስራት ማጣሪያ የተደረገ እና ወቅታዊ የልጆች ደህንነት ስልጠና ያካሄዱ ናቸው።
- ልጆች ሲናገሩ እና ሲያዳምጡ ማበረታታት።
- የልጆችን ደህንነት አስፈላጊ ግምት ውስጥ እንዲገባ ማድረግ፤ ይህ ማለት በእያንዳንዱ ውሳኔ ላይ ለልጆች ፍላጎቶች ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው።
- የልጆች በቃል ንግግር ያልሆነ ግንኙነትን በትኩረት መከታተል።
- ከወላጆች ጋር ግልጽ የሆነ ግንኙነትን መፍጠር እና ኣስተያየትን መቀበል።
- የጥራት ደረጃቸውን እና የልጆችን እንክብካቤ ለማሻሻል ምን እያደረጉ እንደሆነ ያሳያል
- በሚጎበኙበት ጊዜ ወላጆች የሚያተኩሩት: ለሚከታተሉት ሰራተኞችን፤ ደህንነቱ የተጠበቀ የመጫወቻ ቦታዎችን በእንቅስቃሴዎች ላይ የተሰማሩ ልጆች, እና ስለ ዕለት ተዕለት እና የደህንነት ደንቦች ግልጽ ማብራሪያዎች።

## በ2026 ዓ ም የልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዳዲስ ህጎች

የብሔራዊ የጥራት ጥበቃ ማእቀፍ የህጻናት እንክብካቤ ማእከላት እንዴት እንደሚሠሩ ደንቦችን ያስቀምጣል። በ 2026 ዓ›ም የልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ አዳዲስ ደንቦች ቀርበዋል። እነዚህ በሜልበርን ውስጥ ጨምሮ በቅርብ ጊዜ በልጅነት ጊዜ ትምህርት እና እንክብካቤ በልጆች ላይ ለደረሰው ጉዳት ምላሽ ለመስጠት የሚያስተዋውቁ ናቸው።

---

**1** **በእያንዳንዱ ውሳኔ ውስጥ የልጆች ደህንነት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል**

‘ዋና ግምት የሚሰጠው’ በአዲስ ደንብ ሲሆን ይህም ማለት በቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎት ውስጥ የሚሰራ ወይም የሚያካሂድ እያንዳንዱ ሰው በሚወስነው ውሳኔ ሁሉ ’የልጆችን ደህንነት፣ መብቶች እና ፍላጎት ጥቅማቸውን ማስቀደም አለበት ማለት ነው። ይህ ስለ የሰራተኛን ምደባ፣ ቁጥጥር እና ስጋቶች እንዴት መልስ እንደሚሰጡ ውሳኔዎችን ያጠቃልላል።

**2** **ሁሉም ሰራተኞች እና በጎ ፈቃደኛ ሰራተኞች የልጆች ደህንነት ሥልጠና ማጠናቀቅ**

አዲስ ደንቦች ከልጅዎ ጋር በህጻናት እንክብካቤ ውስጥ የሚሠራ እያንዳንዱ ሰው በልጆች .ደህንነት ላይ ልዩ ሥልጠና መውሰድ እንዳለበት ይገልጻል።

**3** **በልጆች ዙሪያ የግል ስልኮች እና መሳሪያዎች አይፈቀዱም።**

ሰራተኞች2]ከ ልጆች ጋር በቀጥታ በሚሰሩበት ጊዜ ፎቶግራፎችን ወይም ቪዲዮዎችን ማንሳት የሚችሉ የግል ስልኮች ወይም መሳሪያዎች እንዲኖራቸው አይፈቀድላቸውም። የልጆችን ፎቶ ለማንሳት በአገልግሎት የተፈቀዱ መሣሪያዎች ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

**4** **በኣሁን ጊዜ በልጅ ዙሪያ ተገቢ ያልሆነ ባህሪ መፈጸም ከባድ ወንጀል ነው**

አሁን ለማንኛውም መደበኛ ወይም የበጎ ፈቃደኛ ሰራተኛ  አንድ ምክንያታዊ የሆነ ሰው ተገቢ አይደለም ብሎ በሚያስበው መንገድ ለልጅ ባህሪ ማሳየቱ ከህግ ውጭ ነው። የተፈቀደላቸው አቅራቢዎች እና ተቆጣጣሪዎች በእነሱ እንክብካቤ ስር ያለ ማንኛውም ልጅ ለእንደዚህ ዓይነት ባህሪ እንዳይጋለጥ ማረጋገጥ አለባቸው። ተገቢ ያልሆነ ባህሪ እንደ ልጆችን መሳም፣ ልጅን ልዩ ትኩረት መስጠት ወይም ልጆች ሚስጥር እንዲጠብቁ መጠየቅ ያሉ ድርጊቶችን ያጠቃልላል። ስለ አስተማሪው ባህሪ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ያለዎትን ስጋት የማንሳት መብት አለዎት።

**5** **አላግባብ በደል ሲፈጸም በ24 ሰዓታት ውስጥ ለተቆጣጣሪው ሪፖርት መደረግ**

በአገልግሎት ላይ በልጅ ላይ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት የሚፈጸም ክስተት ወይም ክስ ካለ፣ አገልግሎቱ በ24 ሰዓታት ውስጥ ለ VECRA ሪፖርት ማድረግ አለበት። VECR A የህጻናት እንክብካቤን ዘርፍ ይቆጣጠራል እናም በስጋቶች ላይ በፍጥነት እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

### ይህ ለወላጆች ምን ማለት እንደሆነ

እነዚህን ደንቦች እንዴት እንደሚያስቀምጡ አገልግሎትዎን መጠየቅ ይችላሉ። ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት የነዚህ ንማብራራት ማቅረብ ይችላል።



## ገና በልጅነት ጊዜ ለፎቶግራፍ እና ምስልን ለመውሰድ ስምምነት

በአውስትራሊያ ውስጥ ስለ ስምምነት (ፈቃደኝነት) እንነጋገራለን። ስምምነት ማለት የአንድን ሰው ፎቶ ከማንሳት ወይም ከማጋራት በፊት ፈቃድ መጠየቅ እና ያላቸውን ምላሽ ማዳመጥ ማለት ነው።

ልጆች በቅድመ ልጅነት ጊዜ ትምህርት እና እንክብካቤ ለመማር ሲባል እና ለሰነዶች ፎቶግራፍ ሊነሱ ይችላሉ። አገልግሎቶቹ ፎቶዎች እንዴት እንደሚነሱ፣ እንደሚቀመጡ እና እንደሚጋሩ ግልጽ ደንብ ህጎች ሊኖራቸው ይገባል። ሰራተኞቹ የልጆችን ፎቶ ለማንሳት ብቻ በማእከሉ የጸደቁ መሳሪያዎችን መጠቀም አለባቸው። የግል ስልኮች ወይም የግል መሳሪያዎች ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም። ወላጆች ብዙውን ጊዜ በምዝገባ ላይ ለፎቶዎች እና ቪዲዮዎች ፈቃድ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ፣ ይህም እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ወይም እንደሚጋሩ ጨምሮ ፈቃድ ይጠየቃሉ። ብዙ አገልግሎቶች ወቅታዊ የሆነን፣ የመማሪያ ታሪኮችን እና ፎቶዎችን ከቤተሰቦች ጋር ለማጋራት ደህንነቱ የተጠበቀ ዲጂታል መድረኮችን ይጠቀማሉ። እንዲሁም ወላጆችም ምስሎች እንዴት እንደሚቀመጡ እና ማን ማየት እንደሚችል የማወቅ መብት አላቸው። ወላጆች የሁሉንም ልጆች’ ግላዊነት ለመጠበቅ የራሳቸውን ጨምሮ በማእከሉ ውስጥ ያሉ ልጆችን ፎቶ ማንሳት የለባቸውም።

### ሊጠይቋቸው የሚገቡ ጥያቄዎች አጭር ዝርዝር እነሆ

- የልጄ ፎቶዎች እንዴት ይነሳሉ?
- ፎቶግራፎችን ከማንሳትዎ በፊት የልጄን ፈቃደኛ መሆን ይጠይቃሉን?
- የልጄ ፎቶዎች የት ነው የተቀመጠው ታዲያ ማን ሊያገኘው ይችላል?
- ፎቶዎች በግል ስልኮች ላይ እንዳይቀመጡ እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል?
- ፎቶዎችን እና መልእክቶች ለማጋራት የትኞቹን መተግበሪያዎች (apps) ወይም መድረኮች/platforms ይጠቀማሉ?
- በእነዚህ መድረኮች ላይ የልጄን ፎቶዎች ማን ማየት ይችላል?

**የወላጅ ቅጂ**

“አንድ ሰው የእርስዎን ፎቶ ማንሳት ሲፈልግ መጀመሪያ ሊጠይቅዎት ይገባል። እርስዎአዎ ወይም አይሆንም ማለት ይችላሉ።  የኣንተሰውነት የራስህ ነው፣ እናም የአንተ ፎቶዎች እና ቪዲዮዎች የአንተው ናቸው።”



### ልጆች ወሲባዊ ጥቃት በኢንተርነት መስመር (ኦንላይን) ላይ

አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው ወሲባዊ ወይም ጎጂ የሆኑ የልጆችን ፎቶዎች ወይም ቪዲዮዎች ሊያነሳ ወይም ሊያጋራ ይችላል። ይህ ከባድ ወንጀል ነው። ይህ የልጆች ወሲባዊ ጥቃት ቁሳቁስ ወይም CSAM ይባላል። አንድ ሰው እንደዚህ አይነት የልጆችን ምስሎችን በመስመር ላይ ለማግኘት ወይም ለመላክ ሲሞክር ይህ ደግሞ ህገ ወጥ ወንጀል ነው። ይህ የልጆች ወሲባዊ ብዝበዛ ቁሳቁስ ወይም CSEM ይባላል። በልጅዎ ላይ እንደዚህ ያለ ነገር ደርሶ ወይም አንድ ሰው ይህን ለማድረግ እየሞከረ ነው ብለው የሚጨነቁ ከሆነ በድረገጽ **esafety.gov.au** ከሚገኘው የኢሴፍቲ ኮሚሽነር (eSafety Commissioner) እርዳታ ማግኘት ወይም ፖሊስን ማነጋገር ይችላሉ።

ምዕራፍ 2

# ወንድ አስተማሪዎች

ሁሉም አስተማሪዎች ግልጽ፣ አክባሪ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን ሲከተሉ ልጆች በጣም ደህና ይሆናሉ። አንዳንድ ወላጆች ስለ ወንድ አስተማሪዎች ይጨነቃሉ። ደህንነት የሚወሰነው በአዋቂዎች በሚያደርጉት ላይ እንጂ በጾታቸው ላይ አይደለም። ይህ ክፍል ደህንነቱ የተጠበቀ ባህሪ ምን እንደሚመስል እና ወላጆች ምን ሊመለከቱና መገንዘብ እንደሚችሉ ያሳያል።



## ሶስት ሊታዩ የሚችሉ ልምዶች



### 1. የተረጋጋ እና አክብሮት የተሞላበት ባህሪ

- አስተማሪው በተረጋጋ ድምጽ ይናገራል።
- ምን እያደረጉ እንደሆነ ለልጁ ያስረዳሉ።
- ልጆቹ ምቾት ያላቸው ይመስላሉ እናም አይፈሩም።



### 2. ግልጹ የሆኑ ገደቦች እና ቁጥጥር

- አስተማሪው ሌሎች አዋቂዎች ሊያዩዋቸው በሚችሉበት ቦታ ላይ ይቆያል።
- ልጆችን ወደ ድብቅ ወይም የተዘጉ ቦታዎች አይወስዱም።
- ልጅን የሚነኩት ለእንክብካቤ ወይም ለደህንነት ሲያስፈልግ ወይም ህጻኑ ማቀፍ ከጠየቀ ብቻ ነው።
- በልጆች ዙሪያ የግል መሳሪያዎችን አይጠቀሙም።
- ልጆችን ከእድሜያቸው ጋር የሚስማሙ ነገሮችን እንዲያደርጉ ብቻ ይጠይቃሉ።



### 3. የልጁን ምርጫ መደገፍ

- አስተማሪው ህጻኑ ነገሮችን በራሳቸው እንዲያደርጉ ይረዳል።
- እርዳታ ከመስጠት በፊት ልጁን ይጠይቃሉ ወይም ያሳውቃሉ።
- ፎቶ ከማንሳት በፊት ፈቃድ ይጠይቃሉ።
- አንድ ህጻን "አይሆንም" ካለ ወይም ምቾት ያልተሰማው መሆኑን ካሳየ ያዳምጣሉ።

## ሁኔታዎች

### ትክክለኛ ተገቢ ባህሪ

- አስተማሪ ለአንድ ልጅ እጆቹን እንዲታጠብ ይረዳል። 'አሁን እጅህን እንጠብ' ይላል፣ ከልጁ አጠገብ ይቆማል። ሌሎች ልጆች እና ሰራተኞች በአቅራቢያ ይገኛሉ። ልጁ አብሮት ይከተላል እና የተረጋጋ ይመስላል።
- ኣንድ ልጅ ወደ ቦታዉ ሲያመጡት ይናደዳል አስተማሪው በልጁ ቁመት ልክ ተበርክኮ 'ማዘን ይቻላል፣ ምንም አይደለም' ይላል። እናት በኋላ ትመለሳለች።'ለልጁ ለእንቅስቃሴ የሚሆኑምርጫዎችን ያቀርብለታል። ልጁ ቀስ በቀስ ይረጋጋል።

### ጥያቄ ሊፈጥር የሚችል ባህሪ:

- አንድ አስተማሪ አንድን ልጅ መግለጫ ሳይሰጥ አንስቶ ወደ ሌላ ቦታ ይወስደዋል። ልጁ የተበሳጨ ይመስላል እና ለመውረድ ይሞክራል።
- አንድ አስተማሪ ለአንድ ልጅ ብዙ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ብዙውን ጊዜ ይህንን ልጅ ከሌሎች ርቆ ወደ ሚገኝ ጸጥ ወዳለ ቦታ ይወስዳል። ከቤት ኣሻንጉሊቶችን ያመጣላቸዋል እና ህጻኑ ከጓደኞች ጋር እየተጫወተ ባለበት ጊዜ እንኳን ቢሆን ለልጁ አዘውትሮ ያቅፈዋል። ይህንን ያስተዉላሉ እና እርግጠኛ እንዳልሆንክ ይሰማሃል።

## መከታተል የሚገባቸው አደገኛ ባህሪያት።



**አንዳንድ ጊዜ አዋቂዎች ከልጆች ጋር 'ልዩ' ግንኙነቶችን ለመገንባት ሊሞክሩ ይችላሉ። ይህ ደህንነቱ የተጠበቀ አይደለም።**

**ወላጆች የሚከተሉትን መከታተል ይችላሉ:**

- አንድ ልጅ ሚስጥር እንዲይዝ መጠየቅ።
- ለአንድ ልጅ ልዩ ስጦታዎች መስጠት ወይም ከሌሎች ልጆች የበለጠ ትኩረት መስጠት።
- አንድን ልጅ ከሌሎች ጎልማሶች ወይም ልጆች ነጥሎ መውሰድ።
- ለአንድ ልጅ የተለመዱ ደንቦችን ወይም የእለት ተእለት ተግባሮችን አለመከተል።
- ልጁን ለፍቅር መፈለግ።
- ከመጠን በላይ የሆኑ ወይም ተገቢ ያልሆኑ የህጻናት ፎቶዎችን ማንሳት።
- የሌሎች አዋቂዎች ስለ ባህሪያቸው ያላቸውን ስጋት ውድቅ ማድረግ።

## የወላጅቅጂ (ስክሪፕት)

የሆነ ነገር ትክክል እንዳልሆነ ከተሰማዎት፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

“ሁሉም አስተማሪዎች ልጆችን እንዴት እንደሚንከባከቡ መረዳት እፈልጋለሁ። ስለ መንካት እና የክትትል ጥበቃ ህጎችዎን ሊነግሩኝ ይችላሉ?”

“ዛሬ ለእኔ ትክክል ሆኖ ያልተሰማኝ ነገር አስተውያለሁ። ምን እንደሆነእንዲገባኝ ልትረዳኝ ትችላለህ?”

ምዕራፍ 3

# መናገር

አዋቂዎች ሲናገሩ ልጆች ሰህንነት በጣም ይሰማቸዋል። ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ወይም ስጋቶችን ለማንሳት ከባድ እንደሚሆን ሊሰማው ይችላል። ግጭትን ስለመፍጠር መጨነቅ ትችል ይሆናል። መናገር መብትህ ነው። እርስዎን፣ ልጅዎን እና ሌሎች ልጆችን ደህንነት ሊጠብቅ ይችላል።

## ኣራት ደረጃዎች ያለህን ስጋት ለማንሳት

1. የሆነ ነገር ትክክል በማይመስልበት ወይም ስሜት በማይሰጥበት ጊዜ ማስተዋል።
2. ስላስተዋሉት ነገር ከአስተማሪ ጋር ይነጋገሩ።
3. ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና መልሱን ያዳምጡ።
4. አሁንም እርግጠኛ ካልሆኑ፤ ዳይሬክተሩን ያነጋግሩ።



### ማድረግ

- ተረጋጉ እና አክብሮት ይኑርዎት
- ያዩትን ወይም የሰሙትን ይናገሩ
- ለመነጋገር ጸጥ ያለ ጊዜ ይምረጡ
- ለመነጋገር ከልጆች ነጻ የሆነ ቦታ ይምረጡ
- አስፈላጊ ከሆነ ወደ ዳይሬክተሩ ይሂዱ

### ኣለማድረግ

- አይክሰሱ ወይም አይውቀሱ
- ድምጽዎን ከፍ አያድርጉ
- ስጋትዎን ችላ አይበሉ
- የልጆች ደህንነት እንደሚቀድም ኣይርሱ
- ሌላ ሰው ይናገራል ብለው አያስቡ

## የወላጅቅጂ (ስክሪፕት)

### ከአስተማሪ ጋር መነጋገር

"ዛሬ ለእኔ ትክክል ሆኖ ያልተሰማኝ ነገር አስተውያለሁ። ምን እንደተፈጠረ እንድረዳ ልትረዳኝ ትችላለህ?"

### ከዳይሬክተር ጋር መነጋገር

"ስላለኝ ስጋት ከአስተማሪ ጋር ተነጋገርኩ፣ ግን አሁንም እርግጠኛ አይደለሁም። ስለዚህ ጉዳይ አብረን መነጋገር እንችላለን?"

**ማንነታችሁ እንዲታወቅ ካልፈለጋችሁ ስምህን በኢሜይል ወይም በስልክ ሳታጋራ ስጋታችሁን ማንሳት ትችላላችሁ፤ ማንነታችሁ እንዳይታወቅ መጠየቅ ይቻላል።**

"ጤና ይስጥልኝ፣ ስለ ልጆች እንዴት እንደሚንከባከቡ ስጋቴን ማካፈል እፈልጋለሁ። ማንነቴ እንዳይገለጽ እመርጣለሁ፣ ነገር ግን ይህንን እንድትመለከቱት እፈልጋለሁ።"

"አንድ ስጋት ለማካፈል ስልክ እደውላለሁ። ስሜን መስጠት አልፈልግም።"

### ሌሎች ወላጆች ተመሳሳይ ስጋትን ካጋሩ

"ጥቂቶቻችን አንድ ነገር አስተውለናል እና እርግጠኛ እንዳልሆንን ይሰማናል። ይህ ብዙውን ጊዜ እንዴት እንደሚስተናገድ ማስረዳት ይችላሉን?"

"አንዳንድ ወላጆች ልጆች ብቻቸውን ወደ አንድ አካባቢ ሲወሰዱ አይተዋል። ለዚህ የእርስዎ ህጎች ምን እንደሆኑ ሊነግሩን ይችላሉ?"



ምዕራፍ 4

# በአውስትራሊያ የቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ ላይ ደንቦች

ወላጆች የሚፈቀደውንና የማይፈቀድን ነገር ሲያውቁ እና በቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ ውስጥ ምን እንደሚፈቀድና የማይፈቀድን ሲያውቁ ልጆች በጣም ደህና ናቸው። አውስትራሊያ የልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ ጠንካራ ህጎች አሏት። እነዚህ ደንቦች ከሌሎች አገሮች ሊለያዩ ይችላሉ።

## ኣራት ነገሮች ወላጆች ማወቅ ያለባቸው

1. ልጆች ሁልጊዜ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል
2. አስተማሪዎች ልጆችን እንዴት እንደሚንከባከቡ ግልጽ መስፈርቶችን መከተል አለባቸው።
3. ወላጆች ጥያቄዎችን የመጠየቅ እና ግልጽ የሆነ መልስ የማግኘት መብት አላቸው።
4. የልጆች ምስሎች እና ግላዊነት በማንኛውም ጊዜ መጠበቅ አለባቸው

### በልጆች እንክብካቤ ውስጥ አካላዊ ፍቅር

**ማድረግ**

- አንድን ልጅ በሚያስፈልገው ጊዜ እንደ መርዳት፣ መምራት ወይም ለማጽናናት ማቀፍ የመሳሰለ ረጋ ያለ እንክብካቤዎች ምንም ችግር የለውም።
- አስተማሪዎች አንድ ልጅ ለመንካት ደህና ከሆነ መጠየቅ ወይም ማረጋገጥ አለባቸው።
- አካል ጉዳተኛ ልጆች ተጨማሪ ድጋፍ ሊፈልጉ ይችላሉ። አሁንም በፈቃደኝነት እና ደህንነቱ በተጠበቀ እና በአክብሮት የመነካት መብት አላቸው።

**ኣለማድረግ**

- ልጅን መሳም ወይም ያልተፈለገ ንክኪ ማካሄድ ጥሩ ኣይደለም።

### ቅጣት/ተግሳጽ በልጆች እንክብካቤ ውስጥ

**ማድረግ**

- አስተማሪዎች ባህሪን ለመደገፍ የተረጋጉ ቃላትን፣ መመሪያዎችን እና አስተማማኝ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ።

**ኣለማድረግ**

- በአውስትራሊያ ውስጥ በቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ ውስጥ መምታት ወይም አካላዊ ቅጣት ፈጽሞ አይፈቀድም።
- ስለ መምታት ወይም አካላዊ ቅጣት ካዩ ወይም ከሰሙ ዳይሬክተሩን ማነጋገር እና ማብራሪያ መጠየቅ ይችላሉ። አስፈላጊ ከሆነም ስጋቱን ወደ ከፍተኛ ደረጃ መውሰድ ይችላሉ።




### ወላጆች ሊጠይቋቸው የሚችሉ ጥያቄዎች

- ልጆችን ስለመንካት ያለዎትን ህጎች ማስረዳት ይችላሉን?
- የልጆችን ደህንነቱ ያልተጠበቀ (አደገኛ) ባህሪ እንዴት እንደሚቆጣጠሩ ማስረዳት ይችላሉን?
- ፎቶዎችን ስለ ማንሳት እና ስለማጋራት ያለዎትን ህጎች ማብራራት ይችላሉን?





GenWest እና Body Safety Australia የምንሰራበት እና አገልግሎታችንን የምንሰጥበት ቦታ መሬት ሁል ጊዜ የአቦርጂናል መሬት እንደነበረ እና እንደሚሆን ይገነዘባሉ። እኛ ያለፉትን እና የአሁኑን ሽማግሌዎች አክብሮት እንሰጣለን።

በናርም/Naarm፣ በሜልበርን ምዕራብ፣ በኩሊን ብሔር የዉሩንድጄሪ/Wurundjeri እና /Bunurong ህዝብ ላሉት የመጀመሪያ መንግስታት ማህበረሰቦች በኩራት እናደንቃለን። የበለጸገ ልዩነታቸውን፣ ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን እና እውቀታቸውን እና ለዚህ ክልል ህይወት ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እናደንቃለን።

የቅኝ ግዛት ቀጣይነት ያለው ተጽእኖ፣ እንዲሁም የአንደኛ መንግስታት ህዝቦች ጥንካሬ እና ጽናት እንገነዘባለን እና ለመሬት መብት፣ ራስን በራስ የመወሰን እድል፣ ሉዓላዊነት እና ያለፉትን ኢፍትሃዊነት እውቅና ለመስጠት እየተካሄደ ካለው ትግል ጋር አጋርነታችንን እንገልጻለን።